የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 66
ADDIS ABABA, 14th July 2017.

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፱/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለሴቶች የንግድ ስራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጃፓን ዓለም ዐቀፍ የትብብር ድርጅት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ………………………………ገጽ ፱ሺ፯፻፲

## CONTENT

Proclamation NO.1029/2017

Japan International Co-operation Agency Agreement for Financing Women Entrepreneurship Development Program Ratification Proclamation…………………..……………………………page 9710

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፱/፪ሺ፱

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጃፓን ዓለም ዐቀፍ የትብብር ድርጅት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሴቶች የንግድ ስራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፭ ቢሊዮን ፭፻ ሚሊዮን የጃፓን የን (አምስት ቢሊዮን አምስት መቶ ሚሊዮን የጃፓን የን) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጃፓን ዓለም ዐቀፍ የትብብር ድርጅት መካከል የካቲት ፲፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፤-

## PROCLAMATION No.1029/2017

**APROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF JAPAN**

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Japan International Co-operation Agency stipulating that the Agency provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of Japanese Yen 5,500,000,000 (Five Billion Five Hundred Million Japanese Yen) for financing Women Entrepreneurship Development Program was signed in Addis Ababa on the 24th day of February 2017;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on of 22th day of June 2017;

**Now, therefore,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለሴቶች የንግድ ስራ ፈጠራ ብቃት ማሳደጊያ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከጃፓን ዓለም ዐቀፍ የትብብር ድርጅት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፳፱/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መጽደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጃፓን ዓለምዐቀፍ የትብብር ድርጅት መካከል የካቲት ፲፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር ET-P3 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፭ ቢሊዮን ፭፻ ሚሊዮን የጃፓን የን (አምስት ቢሊዮን አምስት መቶ ሚሊዮን የጃፓን የን) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Japan International Co-operation Agency Agreement for Financing Women Entrepreneurship Development Program Ratification Proclamation No.1029/2017".

2. **Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement No ET-P3 signed in Addis Ababa on the 24th day of February 2017 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Japan International Co-operation Agency is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of Japanese Yen 5,500,000,000 (Five Billion Five Hundred Million Japanese Yen) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 14th day of July 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me

www.chilot.me

www.chilot.me